# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ፕላን እና ልማት ቢሮ

## የከተማና የገጠር አስተዳደር እርከን ወሰን ለማካለል የወጣ

## መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 21/2018 ዓ.ም

# መመሪያ ቁጥር 21/2018 ዓ/ም

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕላን እና ልማት ቢሮ የከተማና የገጠር አስተዳደር እርከን ወሰን ለማካለል የወጣ መመሪያ

የብሄራዊ ክልሉን የህዝብ ብዛት፣ የቆዳ ስፋትና መልከአምድራዊ አቀማመጥ ግምት ውስጥ በማስገባት የልማት ስራዎችን የሚያቀናጁ፣ የሚያስተባብሩና የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት ስራዎችን ለማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እንዲያግዙ ታስበው ለሚመሰረቱ ተቋማትና ለሚዘረጉ ፕሮግራሞች ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚሰጡ የተዋረድ አስተዳደራዊ እርከኖችን ማደራጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

በክልሉ መንግሥት ለተደራጁ አስተዳደራዊ እርከኖች እንዲሁም የወረዳዎችና ቀበሌዎች ይከፈሉልን ጥያቄዎችን ለሚያቀርቡ አካባቢዎች የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የአስተዳደር ወሰን፣ መለያ ኮዶችን በመስጠት የካርታ ሥራ እንዲሠራ፣ የሥነ-ሕዝብ መረጃዎችን እንዲያደራጅ እና ለተጠቃሚዎችም የማሰራጨት ኃላፊነት በሕግ የተሰጠው በመሆኑ፤

የከተሞች እድገት እና ለውጥ ጉዳይ ከገጠር አስተዳደር አካላትና ሌሎች ተቋማት ጋር ተናቦ መስራትና ንቁ ተሳትፎን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ የተቋማትን ቅንጅታዊ አሠራርና የየራሳቸዉን መረጃዎች ወጥ በሆነ መልኩ ለማደራጀት፣ ለመተንተንና ለተጠቃሚ አካላት ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ከተሞች የማደግና የመስፋፋት ፍላጎታቸውን በረጅምና አጫጭር ጊዜያት እቅዶች እንዲያሳኩ ለማድረግ የከተሞችን የወሰን ማካለል ሥራዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ መምራት በጽኑ የሚታመን በመሆኑ፤

ከተሞች የአስተዳደራዊ ወሰናቸውን ለማስፋፋት ሲፈልጉ የሚካተቱት ወረዳዎችና ቀበሌዎች ነዋሪዎችን ፍላጎትና ውሳኔ መሠረት ያደረገ፣ በበቂ ምክንያት አሳማኝ እና ፍትሓዊ በሆነ መንገድ ወደ ከተሞች የመካተት ሂደቱን በማከናወን ቀበሌዎቹ ትክክለኛ አሠራርን ተከትለው ወደ ከተሞቹ እንዲካተቱ የሚያስችል መመሪያ ማውጣት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ በአዲሱ የአስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ሥልጣን እና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 300/2017 አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 26 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላን እና ልማት ቢሮ የከተማና የገጠር አስተዳደር እርከን ወሰን ለማካለል የወጣ መመሪያ ቁጥር 21/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1/ **"ምክር ቤት"** ማለት እንደ አግባብነቱ የአማራ ክልል መስተዳድር፣ የብሄረሰብ አስተዳደሮች፣ የከተማ አስተዳደሮች፣ የወረዳ እና ቀበሌ አስተዳደሮች ምክር ቤት ነው፤

2/ **"ከንቲባ"** ማለት በከተማው ምክር ቤት አማካኝነት የሚመረጥ ሆኖ የከተማውን ፖለቲካ ፣ አስተዳደር ፣ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች በበላይነት የሚመራ ዋና ስራ አስፈፃሚ ነው፡፡

3/ **"ከተማ"** ማለት ሁለት ሺህና ከዚያ በላይ የሆነ ህዝብ በአንድ ላይ ተሰባስቦ የሚኖርበትና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በሚያወጣቸውመመዘኛዎች መሠረት ክልሉ "ከተማ" ብሎ የሚሰይመው ማናቸውም አካባቢ ነው፤

4/ **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት በክልሉ ውስጥ ተለይቶ በታወቀ መልክዓ-ምድራዊ ወሰን የተደራጀና የአንድን ከተማ ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥልጣንና ኃላፊነቶችን ተረክቦ የሚመራ የአካባቢ አስተዳደር ነው፡፡

5/ **"የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ** አስተዳደር" ማለት የአንድን ከተማ ሁለንተናዊ ልማት ከማፋጠን አንፃር ዓይነተኛ ማዕከል በመሆን በዙሪያው የሚገኙትን አነስተኛ ከተሞች ይዞ ወይም አጠቃሎ እንዲያድግ ለተመረጠ ለማናቸውም የክልሉ ከተማ የተሰጠ መጠሪያ ነው፡፡

6/ **"ክፍለ -ከተማ"** ማለት በሪጂዮ -ፖሊታንና እንደ ከተማው የዕድገት ሁኔታ በፈርጅ አንድ ስር በሚጠቃለሉ ከተሞች ውስጥ ከከተማ አስተዳደር ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

7/ **"የዞን አስተዳደር"** ማለት በክልሉ ውስጥ ተለይቶ በታወቀ መልክዓ-ምድራዊ ወሰን የተደራጀና የአንድን ዞን ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥልጣንና ኃላፊነቶችን ተረክቦ የሚመራ የአስተዳደር እርከን ነው፤

8/ **“የወረዳ አስተዳደር”** ማለት በክልሉ በተደራጀ የዞን አስተዳደር ውስጥ ተለይቶ በታወቀ መልክዓ-ምድራዊ ወሰን የተደራጀና የአንድን ወረዳ ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ፣የአስተዳደር፣ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥልጣንና ኃላፊነቶችን ተረክቦ የሚመራ የአስተዳደር እርከን ነው፤

9/ **“ቀበሌ”** ማለት በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ ድንበሩ በግልፅ የሚታወቅና የራሱ ህጋዊ አመራር ያለው የክልሉ ዝቅተኛው አስተዳደር እርከን ነው፤

10/ **“የከተማ ቀበሌ”** ማለት በከተሞች ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ነው፤

11/ **“የገጠር ቀበሌ”** ማለት በወረዳ ውስጥ በገጠር አካባቢ የሚገኝ ዝቅተኛ የአስተዳደር አካል ነው፤

12/ **“በከተማ አስተዳደር የተጠቃለለ የገጠር ቀበሌ”** ማለት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የከተማነት ደረጃ በሰጠው በየትኛውም ከተማ ወሰን የተካተተ ወይም የታቀፈ የገጠር ቀበሌ ነው፤

13/ **“የአስተዳደር እርከን”** ማለት በማናቸውም በከተማ እና በገጠር ውስጥ የህዝብ ብዛትን መሰረት በማድረግ የተዋቀረ የተዋረድ የአስተዳደር ደረጃ ነው፤

14/ **“የከተማ ፕላን”** ማለት ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀና ህጋዊ ተፈፃሚነት ያለው የከተማ መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን ወይም መሠረታዊ ፕላን ሲሆን አባሪ የፅሁፍ ማብራሪያዎችን ይጨምራል፤

15/ “የከተማ አስተዳደር ወሰን” ማለት ለአንድ ከተማ በከተማ ፕላን መሠረት ለተወሰነ የፕላን ዘመን በካርታ ተከልሎ የተሰጠውና በቀጥታ በከተማ አስተዳደሩ ሥልጣን ሥር ሆኖ የሚተዳደር የከተማው የመሬት አጠቃቀም እና ከሌላው አጎራባች የገጠር ዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር ጋር የሚዋሰኑበትን ወሰን ይጨምራል፤

16/ **“የአስተዳደር ማዕከል”** ማለት ለክልል፣ ለዞን፣ ለወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደሮች አስተዳደራዊ መቀመጫነት የሚያገለግል ከተማ ነው፤

17/ **“የገጠር ማዕከል”** ማለት በጥናት ተደግፎ በነዋሪው ህዝብ አስተያየት አግባብ ባለው የወረዳ አስተዳደር በኩል ለመኖሪያነትም ሆነ ለሌሎች የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አገልግሎቶች የተመረጠ ቦታ ነው፤

18/ **“የቆዳ ስፋት”** ማለት የአስተዳደር እርከኖች በሕግ አግባብ ተለይቶ የሚያስተዳድሩት እና የተከለለ የአስተዳደር ወሰን ያለው በስኩየር ኪሎ ሜትር ወይም በሄክታር የሚገለፅ የአስተዳደር አካባቢ ነው፤

19/ **"የአስተዳደር ወሰን"** ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ቀበሌዎች አንዱ ከሌላው ጋር የሚዋሰኑበት ወሰን ነው፤

20/ **"ካርታ"** ማለት መሬት ላይ የሚገኙትን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሆኑ ገፅታዎችን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አነስተኛ በሆነ መልኩ እንዲያሳይ አድርጎ በማዘጋጀትና በማስፈር የማሳየት ዘዴ ነው፤

21/ "የአየር ላይ ራዲዬስ" ማለት በመስፈርቱና በስታንዳርዱ መሠረት ከአንድ ከተማ ማዕከል ተነስቶ በሚጠይቀው ልኬት መሠረት በወፍ በረር የመለካት ዘዴ ነው፤

22/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው

23/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሁሉ የሴትንም ጾታ ይመለከታል።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ ውስጥ በተቋቋሙ ወይም በሚቋቋሙ ዞኖች፣ ሪጂ-ፖሊታን ከተሞች፣ የከተማ አስተዳደሮች፣ የገጠር ወረዳዎች እንዲሁም በክልሉ የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 4. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1/ በክልሉ የከተሞች የአስተዳደር ወሰን ለማካለል እና ቀበሌዎችን ለማቋቋም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በወሰን አከላለል እና ቀበሌ ከማቋቋም ጋር ተያይዞ የሚታዩ ዋና ዋና ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት፤

2/ ከተሞች የአስተዳደር ወሰኖቻቸውን ለማካለል እና ቀበሌዎችን ለማቋቋም የሚመለከተው አካል ወቅታዊ፣ ታማኝነቱን የጠበቀና ወጥ የሆነ ግንዛቤና መረጃ በመያዝ የወሰን ማካለል እና የቀበሌ ማቋቋም ሥራዎችን እንዲሰራ ለማስቻል፤

3/ ዞኖችን፣ ከተሞችን እና ወረዳዎችን በሚያሳድግ ሁኔታ ለማስተዳደር የሚያስችል አቅም ለመፍጠር፤

4/ በአስተማማኝ መረጃ ላይ በመመስረት የወሰን ይካለልልን ጥያቄዎችን በወቅቱና በጥራት ለማካለል የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎችን በማሟላት ረገድ ሀላፊነት ያለባቸው አካላት ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል፤ እንዲሁም ሚናቸውን በአግባቡ በማይወጡት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለማስወሰድ።

## 5. መሠረታዊ መርሆዎች

1/ **የነዋሪዎችን የመወሰን መብት ማክበር፦** የወሰን መወሰን ሂደት የህዝብ ተሳትፎን፣ ባህል፣ ቋንቋ እና የአካባቢ ማንነቶችን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን፤

2/ **የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን ማክበር፦** በወሰን መወሰን ሂደት ውስጥ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት፣ተሳትፎ፣ ፍትሃዊነት እና የሕግ የበላይነት መከበር አለባቸው።

3/ **የጂኦግራፊያዊ ቅርበት እና ተደራሽነትን ከግምት ማስገባት፦** የአስተዳደር ወሰኖች በቀላሉ ተደራሽ እና አገልግሎቶችን በብቃት ለመስጠት የሚያስችሉ እንደ የተፈጥሮ መልከዓ ምድር፣ የአካባቢ ማእከላት እና መንገዶች ተደራሽ መሆን አለባቸው።

4/ **የህዝብ ብዛት እና ኢኮኖሚያዊ አቅምን ከግምት ማስገባት፦** በቂ ሀብት፣ መሠረተ ልማት እና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለማረጋገጥ **የህዝብ ብዛት እና ኢኮኖሚያዊ አቅም** ግምት ውስጥ መግባት አለበት፤

5/ **የታሪክ እና ባህላዊ ትስስርን ከግምት ማስገባት፦** - የአካባቢው ሕዝቦች ታሪካዊ እና ባህላዊ ትስስር የአካባቢውን ማንነት እና ማህበራዊ አወቃቀር ለመጠበቅ ግምት ውስጥ መግባት አለበት፤

6/ **የልማት እና የአገልግሎት ተደራሽነት፦** የልማት ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ መሠረተ ልማት በተመጣጣኝ ሁኔታ ለማሰራጨት ትኩረት መስጠት አለበት፤

7/ የፖለቲካ እና የጸጥታ መረጋጋትን ከግምት ማስገባት፦ የወሰን ማካለል ሂደት ግጭቶችን በማያባብስ ወይም አዲስ የይገባኛል ጥያቄዎችን በማያስነሳ አግባብ መከናወን አለበት።

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>ስለከተሞች፣ የገጠር አስተዳደር ወረዳዎችና ቀበሌዎች ወሰንና አከላለል</u>

## <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

## <u>ስለከተሞች ወሰን አከላለል</u>

### <u>6. ስለከተሞች ወሰን</u>

1/ የሪጂዮፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች ወሰን ከማዕከላዊ የከተማው ስፍራ በመነሳት፦

ሀ). በዙሪያው እስከ 30 ኪሎ ሜትር የአየር ራዲየስ የሚገኘውን መልከዓ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚገኘውን ነዋሪ ሕዝብ፣

ለ) በአማካይ እስከ 30 ኪሎ ሜትር ራዲየስ የሚገኙ ወሰናቸው የተለየ የአካባቢ አስተዳደር አቋም ያላቸው ከተሞችንና በውስጣቸው የሚገኘውን ነዋሪ ሕዝብ ያጠቃልላል።

2/ የመካከለኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን ከየከተሞቹ ማዕከላዊ ስፍራ በመነሳት በዙሪያቸው እንደ ሁኔታው 15 ኪሎ ሜትር የአየር ርቀት ራዲየስ ዙሪያ ያለውን መልከዓ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ህዝቦችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

3/ የአነስተኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን ከየከተሞቹ ማዕከላዊ ስፍራ በመነሳት በዙሪያቸው እንደ ሁኔታው 5 ኪሎ ሜትር የአየር ርቀት ራዲየስ ዙሪያ ያለውን መልከዓ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ሕዝቦችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

## 7. ስለከተሞች ወሰን አከላለል

1/ የከተሞችን ወሰን የማካለል ስራ በከተሞች የማደግ፣ የመስፋፋት እና የመልማት ፍላጎቶችን በዘላቂነት ለመምራት በሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው አጠቃላይ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ የማካለል ሥራው፦

ሀ) ከዚህ በፊት ተግባራዊ ሲደረጉ የነበሩ አሠራሮችን ክፍተት በመሙላት እና

ለ) አዳዲስ አዳጊ ሀሳቦችን በመጨመር ይሆናል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማ ወሰን ሲካለል የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ማስገባት አለበት፡-

ሀ) የከተማ ወሰን እንዲካለልለት የጠየቀው ከተማ ወይም የገጠር ቀበሌ የወሰን ማካለሉ ሥራ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ኮሚቴ እና ቀበሌውን የሚያስተዳድረው የወረዳ መስተዳደር ምክር ቤት ተስማምተው በቃለ-ጉባኤ ያረጋገጡ መሆኑን፣

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሀ. የተገለጹት አካላት የውሳኔያቸውን ቃለ-ጉባኤ ጉዳዩ በተጀመረ በሁለት ወር ውስጥ አሟልተው ለክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ያደረሱ መሆኑን፤

4/ በከተሞች እድገት ምክንያት ከአዋሳኝ ወረዳዎች በተደነገገው ርቀት ውስጥ የሚገኙትን ቀበሌዎችን ማካተት ይቻላል፡፡ ሆኖም በማናቸውም ምክንያት በቅርበት የሚገኙ አዋሳኝ ቀበሌዎችን በመዝለል ሌሎችን ማካተትና ማካለል አይቻልም ፡፡

5/ ማንኛውም ቀበሌ ወደ ከተማ እንካለል ጥያቄ ሲያቀረብ እና ጥያቄው ተቀባይነት ሲኖረው ቀበሌውን ሙሉ በሙሉ እንጅ በከፊል ወደ ከተማው ማካተት አይቻልም፡፡ ሆኖም ቀበሌውን ሙሉ በሙሉ ወደ ከተማው ለማስገባት የመልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ እንቅፋት የሚኖረው ከሆነ ለክልል መስተዳድር ምክርቤቱ ቀርቦ ጉዳዩ ታምኖበት ውሳኔ ሲያገኝ ቀበሌው በከፊልም ቢሆን ወደ ከተማው ሊካለል ይችላል፡፡

6/ ከተሞች እድገታቸውን ጠብቀው አጎራባች ቀበሌዎችን በማካተት የአስተዳደራዊ ወሰናቸውን ለማሳደግ ሲጠይቁ ወደ ከተማዎቹ የሚካተቱት ቀበሌዎችና ሲያስተዳድሯቸው የነበሩት ወረዳ አስተዳደሮች ወይም ቀበሌ አስተዳደሮች የቀበሌዎቻቸውን ሕዝብ ፍላጎት መሠረት አድርገው ወደ ከተሞች የመካተት ሂደቱን ተቀብለው ጉዳዩ በተጀመረ በሦስት ወራት ውስጥ ወደ ከተሞቹ እንዲካተቱ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፤

7/ የከተማ አስተዳደር ማስተር ፕላን ከከተማው ወቅታዊ አስተዳደራዊ ወሰን አልፎ ሲገኝ በከተማው እና በገጠር ወረዳው መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን ለማስቀረት የከተማው ማስተር ፕላን ከመሰራቱ በፊት በዙሪያ የገጠር ወረዳዎች ጋር በመነጋገር ቀጣይ ከተማው ሊያድግበት በሚችለው መልኩ በመነጋገር ማሰራት ይኖርባቸዋል፤

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት አለመግባባቶችን በራሳቸው የሚፈቱ ካልሆነ ከተማው እና የገጠር ወረዳው የሚገኝበት ዞን አስተዳደር ሁለቱን አካላት በማነጋገር እልባት መስጠት ይኖርበታል፤

9/ ይህ መመሪያ ከመፅደቁ በፊት የማናቸውም ከተማ አስተዳደር ማስተር ፕላን ከከተማው ወቅታዊ አስተዳደራዊ ወሰን አልፎ ሲገኝ የከተማው አዋሳኝ ወረዳዎች በማስተር ፕላኑ የተካተቱትን ቀበሌዎች የከተማው አስተዳደር የእነዚህን ቀበሌዎች ወሰን አካትቶ የማካለል እና የማስተዳደር መብት ይኖረዋል፤ እነዚህን ቀበሌዎች ሲያስተዳድሩ የነበሩ ወረዳዎችም ወደ ከተማ አስተዳደሮች የተካተቱትን ቀበሌዎች በዚህ መመሪያ አሠራር መሠረት የማስረከብ ሀላፊነት አለባቸው፤

10/ አነስተኛ ከተሞች በአየር ላይ 5 ኪሎሜትር ራዲየስ ድረስ ማጠቃለልና ማካለል ይችላሉ፤

11/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 የተመላከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በ5 ኪሎሜትር ራዲየስ ውስጥ ሆነው ወደ ከተማ ያልተካተቱ ነገር ግን ወደ ከተማ አስተዳደሩ የመግባት ፍላጎት ያላቸው አካባቢዎችን በወረዳ መስተዳድር ምክር ቤቶች በማስወሰን ወደ ከተማ አስተዳደሩ አካቶ የማካለል ሥራው የሚሠራ ይሆናል፤

12/ ማንኛውም ከተማ እያደገ ሲመጣ በአዋሳኝ የሚገኙ ቀበሌዎችን በዚህ መመሪያ መሠረት የማካተት መብት ይኖረዋል፤

13/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት በሚደረገው የማካለል ሂደት ወደ ከተማ ሳይካተቱ የቀሩት ቀበሌዎች ቁጥር አንድ ወረዳ በሕግ ሊኖረው ከሚገባው ቀበሌዎች ቁጥር ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ የሚመለከታቸውን አካላት በማማከር እና የነዋሪዎቹን ፍላጎት በማጥናት

ወደ አቅራቢያቸው ወረዳ ወይም ከተማ በማጠቃለል ወሰናቸውን አካልሎ በተካተቱበት ከተማ እንዲተዳደሩ መደረግ አለበት፤

14/ የገጠር ቀበሌዎች ወደ ከተማ አስተዳደር ወሰን ሲጠቃለሉ ቀበሌዎቹን የሚረከበው ከተማ አስተዳደር ለሚረከባቸው የእነዚህ ቀበሌ ነዋሪ ሕዝቦች ማንኛውንም ዐይነት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማትን ማቋቋምና ማደራጀት ይጠበቅበታል፤

15/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 መሠረት የተመላከቱትን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን በአጭር ጊዜ ማቋቋም እና አገልግሎቱን መስጠት አለበት፤

16/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን በአጭር ጊዜ ማቋቋም እና አገልግሎቱን መስጠት ባይችል እነዚህ ቀበሌዎች ቀድሞ የነበሩበት ወረዳ ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት አስፈላጊውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፤

17/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 15 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀበሌዎቹን የተረከበው ከተማ አስተዳደር ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ቢበዛ በሁለት ዓመታት ውስጥ ማንኛውንም አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን አቋቁሞና አደራጅቶ ለተረከባቸው ቀበሌዎች አስፈላጊውን አገልግሎትና አቅርቦት የማሟላት ግዴታ አለበት፡፡

## 8. <u>የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች የቀበሌ አደረጃጀት</u>

1/ የሪጆ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር ከተሞች የሕዝብ ብዛት ከ120,000 እና በላይ በመሆኑ ከተሞች ካላቸው የህዝብ ብዛትና የቆዳ ስፋት አንፃር በሚከተሉት ስልቶች መሠረት ቀበሌዎች ይቋቋማሉ፦

ሀ) ከፍተኛ የህዝብ ጥግግት በሚኖርበት የከተማው ክፍል ለማቋቋም የአንድ ቀበሌ የህዝብ ብዛት ከ15,000 እስከ 20,000 ይሆናል፤

ለ) አነስተኛ ህዝብ በሚኖርበት አካባቢ ያሉ የሪጆዮ-ፖሊታን ከተማ ቀበሌዎችን ለማቋቋም የአንድ ቀበሌ የህዝብ ብዛት ከ5,000 እስከ 10,000 ይሆናል፡፡ ስለሆነም በዚህ ደረጃ ላይ የሚገኙ ከተማ ቀበሌዎች ብዛት በአማካይ ከ16-20 ሲሆኑ ቁጥራቸው ከዚህ መብለጥ የለበትም፤

2/ ከ16 በታችና ከ20 በላይ ቀበሌዎች ያላቸው ከተሞች ከተገኙ ባሉበት የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡

## 9. የመካከለኛ ከተማ አስተዳደሮች የቀበሌ አደረጃጀት

1/ የመካከለኛ ከተማ አስተዳደሮች የህዝብ ብዛት 50,000 እና በላይ በመሆኑ፦

ሀ) የአንድ የከተማ ቀበሌ ህዝብ ከ8,000 እስከ 10,000 ሆኖ በአንድ ቀበሌ የሚደራጅ ይሆናል፤

ለ) በመካከለኛ የከተማ ደረጃ ላይ የሚገኙ ቀበሌዎች ብዛት ቢያንስ 7 ሆኖ ከፍተኛው ከ9 መብለጥ የለበትም፤

2/ ከ7 በታችና ከ 9 በላይ ቀበሌዎች ያላቸው መካከለኛ ከተሞች ከተገኙ ባሉበት የሚቀጥሉ ይሆናል።

## 10. የአነስተኛ ከተማ አስተዳደሮች የቀበሌ አደረጃጀት

1/ የአነስተኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች የህዝብ ብዛት 25,000 እና በላይ በመሆኑ፦

ሀ) የአንድ የከተማ ቀበሌ ህዝብ ከ5000 እስከ 8,000 ሆኖ በአንድ ቀበሌ የሚደራጅ ይሆናል፤

ለ) የአነስተኛ ከተማ የቀበሌ ብዛት ቢያንስ ከ5 የማያንስ ሆኖ ከፍተኛው ከ6 መብለጥ የለበትም፤

2/ የአነስተኛ ከተማ ክልል የአየር ራዲየስ እስከ አምስት ኪሎሜትር የሚያካትት ይሆናል።

## 11. ልዩ ሁኔታ ስለሚስተናገድበት ሥርዓት

በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 8 እስከ አንቀጽ 10 የተመላከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ከተወሰነው ህዝብ ብዛት አንጻር የተለየ ሁኔታ ካጋጠመ ወይም ከበለጠ ወይም ካነሰ ጉዳዩ ለክልል መስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ በጥናት ላይ ተመስርቶ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ተግባራዊ ይሆናል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የገጠር አስተዳደራዊ እርከኖች ስለሚቋቋሙበትና ወሰንን ስለ ማካለል

### 12.የዞን፣ የወረዳና የገጠር የቀበሌ አስተዳደሮች አመሠራረት

1/ የክልሉ መንግሥት የሕዝቡን ብዛት፣ የክልሉን የቆዳ ስፋት፣ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በክልሉ ውስጥ ተጨማሪ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ እርከኖችን ወይም የራስ በራስ አስተዳደራዊ አካባቢዎች ሊያቋቁም ይችላል፤

2/ የዞን፣ የወረዳና የገጠር ቀበሌዎች አደረጃጀቶችን በተመለከተ የይከፈለልኝ ጥያቄ ሲቀርብ የሚከተሉትን መመዘኛ መስፈርቶችን በደረጃ በማስቀመጥ እና ሌሎች የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ ምላሽ ሲሰጥበት ይሆናል፡-

ሀ) የህዝብ ብዛት፤

ለ) ሕዝብን አማክሎ ለመምራት ያለው አመቺነት፤

ሐ) አስተዳደራዊ የቆዳ ስፋት፤

መ) በቀበሌ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማዳረስ እንዲሁም ሰላምን ከማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማትን ከማሳለጥ፣ ነዋሪዎችን ለልማት ከማነሳሳትና የተፈጥሮ ሀብትን ከማልማት አንፃር ያለው አመቺነት፤

ሰ) ከከተሞች ጋር ተቀላቅለው እንዲደራጁ የተወሰኑትን የገጠር ቀበሌዎች ልማትና ለውጥ በፈጣን ሁኔታ ለማስተናገድ ካለው አመቺነት አኳያ፤

ሽ) የገጠር- ከተማ ትስስርን ለማጠናከር ያለው አመቺነት እንዲሁም መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ላይ ራዲየስ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፤

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ተፈጻሚነት የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ የሚያቀርበው ማስረጃ የአስተዳደር እርከን ለማቋቋምም ሆነ በየደረጃው ለሚነሱ የወሰን ማካለል ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ጥቅም ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

### 13.የገጠር አስተዳደር ወረዳዎችና ቀበሌዎች አስተዳደራዊ ወሰንን ማካለል

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 መሠረት በገጠሩ አካባቢ ተለይቶ ለተቋቋመ የአስተዳደራዊ እርከን የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ወሰኑን በማካለል የካርታ መለያ ኮዶችን በመስጠት መረጃዎችን በተደራጀ መልኩ ይሰራል፡፡

2/ በክልሉ የገጠር አስተዳደር እርከኖች ተጎራባች አስተዳደሮች የድንበር አለመግባባት ሲኖራቸው ችግሩ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦሥት ስር በተቋቋመው ኮሚቴ እልባትና ዘለቄታዊ መፍትሄ ከተሰጠው በኋላ የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ወሰኖችን የማካለል ስራዎች ይሰራል፤

3/ በአንድ ወረዳ ውስጥ ሊካተቱ ሲገባቸው በተለያየ ምክንያት በጎረቤት ወረዳ አስተዳደር ስር የሆኑ የገጠር ቀበሌዎች ሲያጋጥሙ አግባብ ላለው አካል አቅርበው ውሳኔ ሲሰጥ የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ወሰኖቻቸውን በመለየት እና የካርታ መለያ ኮዶችን በመስጠት ካርታቸውን የማዘጋጀት ሥራ ይሰራል፤

4/ በክልሉ የገጠር የአስተዳደር እርከኖች የስያሜ ለውጥ ሲደረግ የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ወሰኖቻቸውን እና መለያ ኮዶችን በማረጋገጥ የካርታ ሥራ ይሠራል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆኖ በማናቸውም ጊዜ በዞኖች፣ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የአስተዳደር እርከን በኩል የሚነሱ የወሰን ጥያቄዎችን በማጥናት በሚደረስበት ስምምነት መሠረት የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የወሰን ማካለል ስራዎች ይሰራል፡፡

## 14. <u>የቀበሌ አስተዳደር ስለሚቋቋምበትና እውቅና ስለሚያገኝበት ሥርዓት</u>

1/ የቀበሌ እውቅና ለማግኘት እውቅና እንዲሰጠው የፈለገው ማህበረሰብ ወይም አመራሩ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም ክልል መስተዳድሩ በራሱ ተነሳሽነት የቀበሌነት እውቅና በማጥናት በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ነው፤

2/ የማንኛውም ከተማ ወይም የገጠር ቀበሌ እውቅና ሊያገኝ የሚችለው የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ወስኖ በቀበሌነት ሲያቋቁመው ብቻ ነው፤

3/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የእውቅና ይሰጠን ጥያቄ ማመልከቻውን በተቀበለ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ጥናቱን አጠናቆ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## 15. <u>የቀበሌ ስም ለውጥ ስለማድረግ</u>

1/ የከተማም ሆነ የገጠር ቀበሌ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የስም ለውጥ እንዲደረግለት መጠየቅ ይችላል፤

2/ የአንድ ቀበሌ ስም ለውጥ ማድረግ የሚቻለው፦

ሀ) በቀበሌው ነዋሪዎች የተደረሰው ስምምነት በቀበሌ ምክር ቤት እና

ለ) ቀበሌው ተጠሪ በሆነለት የአስተዳደር እርከን ወይም መስተዳድር ምክር ቤት ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡

## 16. የአዲስ ቀበሌ ማቋቋሚያ መስፈርቶች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 12 ስር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በከተማም ሆነ በገጠር ቀበሌዎችን እንደ አዲስ ለማቋቋም የሚከተሉትን መስፈርቶች ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል፦

1/ የህዝብ ብዛት፤

2/ ሕዝብን አማክሎ ለመምራት ያለው አመቺነት፤

3/ አስተዳደራዊ የቆዳ ስፋት፤

4/በቀበሌ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማዳረስ እንዲሁም ሰላምን ከማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማትን ከማሳለጥ፣ ነዋሪዎችን ለልማት ከማነሳሳትና የተፈጥሮ ሀብትን ከማልማት አንፃር ያለው አመቺነት፤

5/ ከከተሞች ጋር ተቀላቅለው እንዲደራጁ የተወሰኑትን የገጠር ቀበሌዎች ልማትና ለውጥ በፈጣን ሁኔታ ለማስተናገድ ካለው አመቺነት አኳያ፤

6/የገጠር- ከተማ እንዲሁም የከተማ-ገጠር ትስስርን ለማጠናከር ያለው አመቺነት እንዲሁም መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ላይ ራዲየስ ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

## 17. ወደ ከተማ የተካለሉ የገጠር ቀበሌዎች በከተማ ቀበሌነት ስለሚቋቋሙበት ሥርዓት

1/ ሙሉ በሙሉ በከተማ ክልል የተካለሉ የገጠር ቀበሌዎች በከተማ አስተዳደሩ ስር ራሳቸውን የቻለ የቀበሌ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ይደረጋል፤

2/ በከፊል የተካለሉ የገጠር ቀበሌዎች የተወሰኑ አካባቢዎች ወይም ጎጦች እንደ አመቺነታቸው በአንድ ላይ ተጠቃለው በቀበሌ ደረጃ እንዲደራጁ ይደረጋል፤

3/ በከፊል የተካለሉ የገጠር ቀበሌዎች የተወሰኑ አካባቢዎች ወይም ጎጦች እንደ አመቺነታቸው በአንድ ላይ ተጠቃለው በቀበሌ ደረጃ ማደራጀት የማይቻል ሆኖ ከተገኘ ከከተማ ቀበሌዎች ጋር ተዋህደው እንዲደራጁ ይደረጋል፤

4/ በዚህ መመሪያ መሰረት በከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ቀበሌዎች ተጠሪነታቸው ክፍለ ከተማ ለተቋቋመላቸው ከተሞች ለክፍለ-ከተማ አስተዳደሮች፣ክፍለ-ከተማ ባልተቋቋመባቸው ከተሞች ደግሞ ለከተማ አስተዳደሮች ሲሆን በገጠር ወረዳ አስተዳደሮች ስር የሚተዳደሩ ቀበሌዎች ተጠሪነታቸው ለወረዳ አስተዳደሮች ይሆናል።

## ክፍል ሦስት

## የወሰን አከላለል ኮሚቴ አሰያየም እና የልዩ ልዩ አካላት ሥልጣንና ተግባር

### 18.የወሰን አከላለል ኮሚቴ አሰያየም

1/ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የከተማ አስተዳደር ከተሞችን ወሰን የሚከልል ከተለያዩ አካላት የተውጣጡ አባላት የያዘ ኮሚቴ በሚመለከተው ከንቲባ ጽሕፈት ቤት ይሰየማል፤

2/ የኮሚቴ አባላት ስብጥርም፤

ሀ) የፕላንና ልማት ቢሮ /2 ተወካይ/----------------------------------------------ሰብሳቢ፣

ለ) ከተማ አስተዳደር፣ ከንቲባ ጽሕፈት ቤት ------------------------------------ፀሀፊ፣

ሐ) ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ------------------------------------------------አባል፣

መ) ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት ------------------------------------------------አባል፣

ሠ) ወረዳ ከተማና መሰረተ-ልማት ጽ/ቤት ---------------------------------------አባል፣

ረ) የወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት ----------------------አባል፣

ሰ) የወረዳ ገቢዎች ጽሕፈት ቤት ------------------------------------------------አባል፣

ሸ) የወረዳ ሰላምና ፀጥታ ጽሕፈት ቤት ------------------------------------------አባል፣

ቀ) የከተማ አስተዳደሩ ሰላምና ፀጥታ ጽሕፈት ቤት --------------------------አባል፣

በ) ከተማ አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ---------------------------------------------አባል፣

ተ) ወደ ከተማ አስተዳደሩ የተካተቱ የገጠር ቀበሌ አስተዳዳሪዎች------------አባላት፣

ቸ) የወረዳ ፕላንና ልማት ተቋም-------------------------------------------------አባል እና

ኀ) የከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ተቋም------------------------------------አባል ናቸው፡፡

### 19.የኮሚቴው አሰራርና ሀላፊነት

ኮሚቴው የአስተዳደር ወሰን ሲሰራ ፦

1/ ቋሚ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ምልክቶችን /መንገድ፣ ወንዝ፣ ተራሮች ወዘተ) እና በተጨማሪም ካርታዎች፣ ማዕዘን ድንጋይና እና የፅሁፍ መግለጫዎች መሠረት ያደርጋል፤

2/ የማጠቃለያ ሪፖርቱን በካርታ በማስደገፍ ለሚመለከተው ወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ያቀርባል፤

3/ የደረሰበትን ውጤት ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣ በቃለ ጉባኤው ላይም ሁሉም የኮሚቴው አባል እንዲፈርሙ ያደርጋል።

## 20.ስለ ወሰን ጉዳይ ቅሬታ ኮሚቴ እና የሚነሱ አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታ

1/ በወሰን ጉዳይ በሪጅ-ፖሊታን፣ በመካከለኛ፣ በአነስተኛ ከተሞች እና በገጠር ወረዳዎች ወይም ወረዳዎች ከወረዳዎች፣ዞኖች ከዞኖች ጋር አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ወይም የይገባኛል ጥያቄዎች ሲነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት በየደረጃው የሚመለከታቸው የወሰን ጉዳይ ቅሬታ ኮሚቴ የተነሱትን ጉዳዮች በማጥናት የሚመለከታቸውን አካላት በማወያየት እልባት የሚሰጥ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ተደራጅቷል፤

2/ የወሰን ጉዳይ ቅሬታ ኮሚቴ ጉዳዩ በቀረበለት ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ በማጠናቀቅ ውሳኔውን ለክልል ፕላንና ልማት ቢሮ ማሳወቅ አለበት፤

3/ በወሰን ጉዳይ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ችግሩን ሊፈቱ የሚችሉ የኮሚቴ አባላት ስብጥር የሚከተሉትን ያካተተ ይሆናል፦

ሀ) የዞን/ ወይም ወረዳ/ አስተዳዳሪዎች ----------------------------------------------ሰብሳቢ፣

ለ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር መሬት መምሪያ/ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች --------አባል፣

ሐ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር የሠላምና ጸጥታ መምሪያ/ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች--አባል፣

መ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር የፖሊስ መምሪያ/ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች-------አባል፣

ሠ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር ፕላንና ልማት ቡድን ጅ.አይ.ኤስ ባለሙያ----አባል፣

ረ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር ፍትህ መምሪያ/ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች----- አባል፣

ሰ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር ከተማና ልማት ጽሕፈት ቤት -------------------አባል፣

ሸ) የወረዳ ገቢዎች ጽሕፈት ቤት -------------------------------------------------------አባል፣

ቀ) የከተማ ምህንድስና ባለሙያ-----------------------------------------------------------አባል፣

በ) ችግሩ የተከሰተበት ቀበሌ አስተዳደር ሊቀመንበር -----------------------------------አባል፣

ተ) ችግሩ በተከሰተባቸው ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎችሦስት--አባላት፤

ቸ) ችግሩ በተከሰተበት ቀበሌ ውስጥ ተመድቦ የሚሰራ የመሬት ባለሙያ አባል ይሆናሉ።

## 21. የኮሚቴው አሰራርና ሀላፊነት

1/ በየደረጃው የተቋቋመው ኮሚቴ የተፈጠሩትን የወሰን ይገባኛል ጥያቄዎች በተዓማኒነት ያጠናል፤

2/ እውነተኛነት ያላቸውን ቋሚ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ምልክቶችን ማለትም መንገድ፣ወንዝ፣ተራሮች… ወዘተ እና በተጨማሪም ካርታዎች፣ ማዕዘን ድንጋይ፣ የፅሁፍ መግለጫዎችን እንዲሁም እውነተኛ ናቸው የሚላቸውን ግለሰቦች በመረጃና ማስረጃነት ያደራጃል ፤

3/ ባህላዊና ሳይንሳዊ የወሰን ግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመቀመርና በመጠቀም ተግባራዊ ያደርጋል፤

4/ በሰበሰበው መረጃና ማስረጃ መሰረት የኮሚቴው አባላት በተገኙበት የውሳኔ ሀሳቡን በማያሻማ ሁኔታ በቃለ-ጉባኤ ይይዛል፣ በቃለ ጉባኤው ላይም ሁሉም የኮሚቴው አባል እንዲፈርሙ ያደርጋል፣

5/ ኮሚቴው ማጠቃለያ ሪፖርቱን በካርታ እና በጽሁፍ ትንተና በማስደገፍ ለሚመለከተው ክልል/ዞን/ ወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ያቀርባል፡፡

## 22. በኮሚቴው ውሳኔ ስለሚቀርብ ቅሬታ

ማንኛውም የበታች የአስተዳደር እርከን በኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ውሳኔው በተሰጠ አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

## 23. ስለፕላንና ልማት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ ሌሎች ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ የፕላንና ልማት ቢሮ ይህን መመሪያ፡-

1/ የአስተዳደራዊ ወሰን የማካለልና ቀበሌዎችን ለማቋቋም የመምራት፣የማስተባበር፣አቅጣጫዎችን የማስቀመጥ፣ የመመሪያዉን አተገባበር የመከታተል እና የመደገፍ ተግባራትን ያከናዉናል፤

2/ እስከ ታችኛው የከተማና ወረዳ አስተዳደር እርከን ድረስ ስልጠናዎችን በመስጠት እንዲሁም ሌሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎችን በመጠቀም የከተሞች፣ የገጠር ወረዳዎችና ቀበሌዎች ግንዛቤ ያሳድጋል፤

3/ መመሪያዉን ተግባራዊ በማያደርጉ የከተማ፣ የገጠር ወረዳና ቀበሌ አስተዳደሮች ላይ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 24. ስለ የከተሞች፣ገጠር ወረዳዎች እና ቀበሌ አስተዳደሮች ተግባርና ኃላፊነት

1/ ማንኛዉም የከተማ፣ የገጠር ወረዳ እና ቀበሌ አስተዳደር ይህን መመሪያ መነሻ በማድረግ፤

(ሀ)እንደተቋሙ ተጨባጭ ሁኔታ ማንዋል ሊያዘጋጅ ይችላል፤ ወይም እንዳለ በመውሰድ ሊጠቀም ይችላል፣

(ለ) በሁሉም የአስተዳደር እርከንና የሥራ ክፍሎች ተግባራዊ ያደርጋል፣

(ሐ) እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ስልጠናዎችን በመስጠት እንዲሁም ሌሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለ ወሰን አከላለልና ቀበሌ ማቋቋም ግንዛቤ ያሳድጋሉ፤

2/ ማንኛዉም የከተማ፣ የገጠር ወረዳ እና ቀበሌ አስተዳደር፤

(ሀ) ሕጋዊ የወሰን ማካለልና ቀበሌ የማቋቋም ሥራዎችን በቅንነትና ታዓማኒነት የማስተባበር፣ የማስፈጸምና የመፈጸም ኃላፊነት አለበት፣

(ለ) የወሰን ማካለልና ቀበሌ ማቋቋም ተግባራት እንዲካሄዱ የሚተገበሩ ቅድመ- ዝግጅቶችን የማሟላት ኃላፊነት አለበት፣

(ሐ) የወሰን ማካለል ሥራው በፕላንና ልማት ባለሞያዎች ከተፈጸመ በኋላ ሰጭና ተቀባይ አካላት ውሳኔውን ተቀብለው ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፣

(መ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) ቢኖርም ለወሰን ማካለሉና ለቀበሌ ማቋቋም ሥራው በመነሻነት የሚረዱ የቅድመ-ዝግጅት መረጃዎች ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት፣

(ሠ) መሟላት ያለባቸው ሕጋዊ አሠራሮች ከቅድመ-ወሰን ማካለሉና ቀበሌ ማቋቋሙ ሥራ ቀድመው መጠናቀቃቸው ተረጋግጦ የፕላንና ልማት ባለሙያዎች ወደ ቦታዎቹ ሲሄዱ እና ሥራቸውን ሲሰሩ በሂደቱ ባለሙያዎችን የማስተባበር እና የመደገፍ ኃላፊነት አለበት።

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 25. ስለመተባበር ግዴታና ተጠያቂነት

1/ ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ ሙሉ ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት።

2/ በየትኛውም የአስተዳደር እርከን አዋሳኝ ቀበሌዎችን በአሰራሩ መሠረት ለማካተትና ወሰናቸውን ለማካለል በሚያደርጉት ሕጋዊ ሂደት የሚካተቱትን ቀበሌዎች ለከተሞች ወይም ተገቢነቱ ለታመነበት የአስተዳደር እርከን ላለመስጠት የሚደረጉ ቢሮክራሲያዊ ውጣውረዶች የተከለከሉ ናቸው፤ ይህን ባደረጉ አመራሮች ላይ ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን መመሪያ ተፈጻሚ በማያደርጉት አመራሮች ላይ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የባለጉዳዩ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይም የሚመለከተው አካል) መረጃውን አደራጅቶ ለሚመለከተው የሕግ አካል በማቅረብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል።

### 26. ወሰንን ስለማሻሻል

የአንድ ከተማ ወሰን ሊሻሻል የሚችለው፡-

1/ በህዝብ ቁጥር መጨመር እና በከተማ መስፋፋት፤

2/ በከተማ ደረጃ ለውጥና ሽግግር ምክንያት ሲሻሻል፤

3/ በከተማው ዙሪያ የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች በምክር ቤቶቻቸው አስወስነው ወደ ከተማ አስተዳደሩ የእንካተት ጥያቄዎችን ሲያቀርቡ ይሆናል።

### 27. መመሪያውን የማሻሻል ሥልጣን

በጥናት ላይ ተመሥርቶ የፕላንና ልማት ቢሮ በሚያቀርበው ጥያቄ መነሻነት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል።

### 28. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 29. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 30/2018 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ከታህሳስ 30/2018 ዓ.ም

ደመቀ ቦሩ ባህሩ (ዶ/ር)

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕላን እና ልማት ቢሮ ኃላፊ